OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የ2026 ዓ.ም Centering Art & Racial Equity (የሥነ-ጥበብ እና የዘር እኩልነት) የገንዘብ ድጎማ መመሪያዎች

## የገንዘብ ድጎማው አጠቃላይ እይታ

የCentering Art & Racial Equity ፕሮግራም የሲያትል የሥነ-ጥበብ እና ባህል ቢሮ የሲያትል የሥነ ጥበባት እና የባህል ድርጅቶችን የሚደግፍበት ፕሮግራሙ ነው። ይህ ፕሮግራም እነዚያ ድርጅቶች የኪነ ጥበባት ሥነ-ምኅዳሩ የበለጠ ፍትሃዊነትን እና አካታችነትን እንዲላበስ በጋራ እንዲሠሩ ለማነሳሳት ታስቦ የተነደፈ ፕሮግራም ነው። በሲያትል ውስጥ ለሕዝብ ቢያንስ ለሦስት ዓመታት ፕሮግራሞችን ሲያቀርቡ የቆዩ የኪነ ጥበብ፣ የባህል፣ የቅርስ ወይም ቱፊት እና የኪነ ጥበብ አገልግሎት ድርጅቶች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ። ሁሉን አቀፍ፣ ፀረ-ዘረኝነት እና ሰውን ያማከሉ እሴቶችን ማዕከል በማድረግ በንቃት የሚሠሩ የሲያትል ድርጅቶችን ለመደገፍ ቅድሚያ እንሰጣለን።

**ስለ ማመልከቻው፣ ስለ ብቁነት ወይም ስለ ኦንላይን የቴክኒክ ድጋፍ መረጃ እና እገዛ ለማግኘት** የባህል መዋዕለ ንዋይ ስልት አቃጅ/ ስትራቴጂስት የሆኑትን ካቲ ህሲያን (Kathy Hsieh) በ (206) 733-9926 በመደወል ወይም ወደ kathy.hsieh@seattle.gov **ኢሜይል በመላክ ያነጋግሩ።**

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪድዮ በኩል) ጨምሮ እርስዎ በሚፈልጉት ቋንቋ ሊያነጋግሩዎ የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** እርስዎ ብቻ ደውለው የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ጥሪውን የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስከምናገኝ ድረስ ለአፍታ ይጠብቃሉ።

## ማመልከቻ

በኦንላይን ያመልክቱ፡- https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new

የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት ከሌለዎት በተቻለ ፍጥነት ሠራተኞችን ያነጋግሩ።

## የሚያበቃበት ቀን

**ማክሰኞ፣ ኦገስት 5 ቀን 2025 ዓ.ም 5:00 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር**

እባክዎ ማመልከቻዎን ሞልተው ለማጠናቀቅ በቂ ጊዜ እንዲኖርዎ ያድርጉ። ከማብቂያው ቀኑ 5 ፒ.ኤም (ፓሲፊክ) በኋላ ገቢ የሚደረጉ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## ብቁነት

የኪነ ጥበብ፣ የባህል፣ የቅርስ ወይም ቱፊት እና የኪነ ጥበብ አገልግሎት ድርጅቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ ብቁ ይባላሉ፡-

- ዋና አድራሻዎ በሲያትል ከተማ ክልሎች ውስጥ ከሆነ
- የኪነ ጥበብ እና የባህል ተልእኮ ወይም ፕሮግራሞች ያሉዎ ከሆነ ወይም ደግሞ ጉልህ የሆነ የኪነ ጥበብ እና የባህላዊ ፕሮግራም ዝግጅት የሚያዘጋጅ ባህል ተኮር ድርጅት ከሆኑ
- ለሲያትል ነዋሪዎች በኪነ ጥበብ እና በባህል ዝግጅቶች በኩል ቢያንስ ለሦስት ዓመት ያክል ለህዝብ ጥቅም የመስጠት ታሪክ ካለዎት
- የ501(c)(3) ሁኔታ እንዲኖርዎ ባይጠበቅብዎትም የፌደራል ግብር መታወቂያ ቁጥር ግን ካለዎት

- ከብዙ አኳያ የፀረ ዘረኝነት እንቅስቃሴዎችን ለመሥራት ቁርጠኛ አቋም ያለው እና እንቅስቃሴዎችን ያለማቋረጥ እያደረገ የሚገኝ ድርጅት ከሆኑ
- በsmART ቬንቸሮች የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራማችን በኩል ምንም ዓይነት የገንዘብ ድጋፍ ያልተደረገልዎ ከሆነ

## የገንዘብ ድጋፍ

ሽልማቶቹ የሚሰጡት በአጠቃላይ የውጤት ልኬት እና በተለያዩ የማኅበረሰብ ቡድን ፓኔል ላይ የተመሠረቱ ናቸው። የድርጅትዎ የበጀት መጠን እርስዎ የሚሸለሙትን የድጎማ መጠን ለመወሰን በመለኪያነት ወይም እንደ ሁኔታ አይወሰድም። የፕሮግራሙ ግብ ብዛት ያላቸውን ፕሮጀክቶች በመጠነኛ የገንዘብ ድጎማ ለመደገፍ እንጂ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ፕሮጀክቶችን በርከት ያለ የገንዘብ ድጎማ በመስጠት መደገፍ አይደለም። የገንዘብ ድጎማ መጠኑ ድጎማው ለሚሰጥበት **እያንዳንዱ ዓመት ከ$500 እስከ $18,000 ዶላር መካከል** ባለው መጠን ውስጥ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

የገንዘብ ድጎማ ሽልማት መጠኑ ከዓመት ዓመት ሊለያዩ የሚችል ሲሆን፣ መጠኑም የከተማው አስተዳደር ከግብር በሚያገኛቸው ገቢዎች እና የበጀት ሂደቶችን መሠረት ያደረገ ነው። በአሁኑ ጊዜ በከተማ አስተዳደሩ በጀት ትንበያዎች መሠረት የገንዘብ ድጎማው በ2026 ዓ.ም የሚጀምር ቢሆንም፣ በዚህ የማመልከቻ ዑደት ላይ ሙሉ የሦስት ዓመት የገንዘብ ድጎማ ይቀርባል የሚል ዋስትና መስጠት ግን አንችልም።

## የመረጃ ወርክሾፖች

በዚህ የገንዘብ ድጎማ እና እንዴት ምርጥ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ በሚለው ዙሪያ ተጨማሪ ለማወቅ ምናባዊ ወርክሾፕ ይቀላቀሉ። በእያንዳንዱ ወርክሾፕ የመጀመሪያው አንድ ሰዓት ለCentering Art & Racial Equity የገንዘብ ድጎማዎችን ማመልከት ላይ ያተኩራል። የCultural Facilities Fund የገንዘብ ድጎማ ፕሮግራማችንን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ የማወቅ ፍላጎት ካለዎት ሙሉውን 90 ደቂቃ ለመታደም ማቀድ ይኖርብዎታል።

**ወርክሾፕ 1**
ሐሙስ፣ ሜይ 29 ቀን 2025 ዓ.ም ከ10:30 ኤ.ኤም-12:00 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 5/29 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 2 🤟 የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL)፦ አስተርጓሚ ይኖራል**
ሰኞ፣ ጁን 2 ቀን 2025 ዓ.ም ከ2:30–4:00 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 6/2 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 3**
ማክሰኞ፣ ጁን 24 ቀን 2025 ዓ.ም ከ12:00-1:30 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 6/24 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 4**
ረቡዕ፣ ጁላይ 9 ቀን 2025 ዓ.ም ከ1:00-2:30 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 7/9 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ